በዓለ ሃምሳ

ቡዲ/ን አባተ አሰፋ

16/09/2002 ዓ.ም.

ዛሬ የጌታችንና የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤ ማክበር ከጀመርን ሃምሳኛዉ ቀን ላይ ደርሰናል ። ይህ ቀን በዓለ ሃምሳ ተብሎ ይጠራል ። የእለቱ ስያሜ በአንድ በኩል ከአማናዊቷ እለተ ትንሳኤ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያሳለፍናቸውን የእለታት ቁጥር ሲያምለክት በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ እለት የተፈፀመ አንድ ክስተት እንዳለ ይጠቁመናል ።

ወንጌላዊው ቅዱስ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት በዚህ እለት ስለተፈፀመዉ ነገር በዝርዝር ከፃፈው ታሪክ የጌታ አርድእት(120ዎቹ የጌታ ቤተሰቦች) በአንድ ላይ ተሰብስበዉ በነበሩበት ቦታ በሚያስደነግጥ በዐዉሎ ነፋስ ድምጽና በተከፋፈሉ የእሳት ላንቃዎች አምሳያ መንፈስ ቅዱስን እንደተሞሉ በዚህም ጎይል በወቅቱ በቦታው ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች በዓለ ሰዊትን ለማክበር ተሰብስበዉ በነበሩ ሰዎች ሁሉ ቋንቋ መናገር እንደቻሉ እንረዳለን። እንዲሁም በወቅቱ ከነበሩት ሰዎች መሃከል ግማሾቹ የሚሉትን እስኪያጡ ድረስ በተገለጠዉ ተአምር ሲገረሙ እኩሌቶቹ ደግሞ በጠጅ ስካር የሚዘላብዱ መስሏቸዉ መሳታቸዉን፤ በኋላ ግን ሊቀ ሐዋሪያት ቅዱስ ጴጥሮስ ከነብዩ ኢዮኤል የትንቢት ቃል በመጀመር እንዳስተማረና በትምህርቱም ሶስት ሺህ ያህል ሰዎች አምነውና ተጠምቀው ወደ ሐዋርያት ማኅበር እንደተጨመሩ እንረዳለን። ከላይ እንደተገለፀዉ የጌታ ደቀ መዛሙርት መንፈስ ቅዱስን የተሞሉት ሁሉም በአንድ ቦታ ተሰብስበው ሳሉ ነበር። ይህ ግን የሆነዉ ድንገት ባጋጣሚ ሳይሆን ከዚች እለት አስር ቀን በፊት ጌታ ወደ ሰማይ ሳያርግ “ እነሆ እኔ የአባቴን ተስፋ ለእናንተ እልካለሁ ፤ እናንተ ግን ከአርያም ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ። “ ሉቃ. 24፥49 ብሎ አዝዟቸዉ ስለነበር የጌታቸውን ተስፋ መፈጸም በአንድነት ሆነው ይጠባበቁ ነበር። ለወዳጆቹ የሰጠውን ተስፋ የማያስቀር ጌታም በአሥረኛው ቀን ኃይልን ከሰማይ ላከላቸው።

ወንጌላዊው ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን የተሞሉበትን አኳኋን “ ድንገትም እንደአውሎ ነፋስ ያለ ድምጽ ከሰማይ መጣ ፤ የነበሩበትንም ቤት ሞላው። እንደ እሳት የተከፋፈሉ የእሳት ላንቃዎችም ታዩአቸዉ፤በሁሉም ላይ ተቀመጡባቸዉ።” የሐዋ. 2፥2-3 በማለት ገልጾታል ። ለመሆኑ ደቀ መዛሙርቱ ለምን መንፈስ ቅዱስን በሚሰማዉ የዐውሎ ነፋስ ድምጽና በሚታዩ የእሳት ላንቃዎች አምሳል ተሞሉ?ለምን በጽጥታ አልተሞሉም? ብለን እንጠይቅ ይሆናል። ይህ የሆነዉ በወቅቱ በቦታዉ ተሰብስበዉ ለነበሩ የአይሁድ ጥቅም ነዉ። ከላይ በጨረፍታ ለመዳሰስ እንደተሞከው በተለያዩ ክፍላተ ዓለም የሚኖሩ አይሁድ ጌታ በፈቃዱ ተላልፎ በተሰጠባት ዕለት ሲያከብሩት ከነበረው የፋሲካ በዓል ጀምረው ለ50 ቅናት ያህል በኢየሩሳሌም ይሰበሰባሉ። የፋሲካ በዓል ከግብፅ ባርነት ነጻ ለወጡባት ዕለት መታሰቢያ ስትሆን ለተከታዩ 50 ቀናት እዚያው ቆይተው በ50ኛዉ ቀን በአለ ሰዊትን (የአሸት በዓልን) አክብረው ይለያያሉ። በዓለ ሰዊት ከግብፅ ከወጡ በኋላ በከነአን ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ እሸት የበሉበትን ወቅት የሚያስቡበትና በየዓመቱም ከዘሩት ሰብል እሸቱን እየበሉ ስለሰጣቸዉ ምርት እግዚአብሔርን የሚመሰገኑበት በዓል ነው። አይሁድ የደቀመዛሙርቱ አስተምህሮ በሰማያዊ ኃይል እንጂ በሰብአዊ ጥበብ እንዳልሆነ ተረድተዉ ለትምሕርታቸዉ ጆሯቸውን እንዲሰጡ ደቀመዛሙርቱ ሰማያዊ ጎይልን ሲቀበሉ ለነሱ በሚታይና በሚሰማ ተአምራዊ ምልክት አደረገላቸዉ። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ አይሁድ ከዚህ ሁሉ ተአምር በኋላ እንኳን ደቀመዛሙርቱ በአንድ ቋንቋ እየተናገሩ ነገር ግን እነርሱ በየሃገራቸው ቋንቋ ማዳመጣቸውን የደቀመዛሙርቱ ስካር ነዉ ካሉ የተደረገውን ተአምር(የመንፈስ ቅዱስን በሚያስደነግጥ መልኩ መሰጠት) ባያዩማ ምን ባሉ ነበር በማለት የአይሁድን ልበ ደንዳናነት ያታዘባል።

መንፈስ ቅዱስን ተሞሉ ማለት ምን ማለት ነው?

በምሥጢረ ሥላሴ አስተምህሯችን መሠረት መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እኩል የሚመለክ ሲሆን የራሱ የሆነ እኔ ባይ አካልም አለዉ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ነው። ታዲያ ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ተሞሉ ወይንም በደቀመዛሙርቱ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፤ አደረባቸዉ ሲባል ያ አካላዊ መንፈስ ወርዶ አደረባቸዉ ማለት አይደለም ። ነገር ግን እግዚአብሔር ጸጋዉን አሳደረባቸዉ ማለት ነው። ይህ ጸጋ የጎይል፣ የብርታት ምንጭ

ስለሆነም ጸጋው በሚያስገኘዉ ውጤት “ ከአርያም ኀይልን እስክትለብሱ” (ሉቃ. 24፥ 49) ተብሎ ተገልጿል።

ደቀመዛሙርቱ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ማግኘታቸውን በአትኩሮት ስንነጋገር ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከነሱ በፊት ከነበሩ ሰዎች ፈጽሞ ርቆ ነበር ለማለት ግን አይደለም። ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ተራዳኢነት ከፍጡራን ሙሉ በሙሉ ከተለየ የፍጡራን ሕያዉነት ያከትማልና። ቅዱሳት መጻሕፍት የመንፈስ ቅዱስ ተራዳኢነት በዘመነ ብሉይ ከነበሩ ሰዎች ጋርም እንደነበረ ይመሰክራሉ። ለምሳሌ ቅዱስ ጴጥሮስ ስለቅዱሳን ነቢያት አገልግሎት ሲናገር “ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣም ። ዳሩ ግን ቅዱሳን ሰዎች ከእግዚአብሔር ተልከው በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝተው ተናገሩ።” 2ኛ ጴጥ.1፥21 ማለቱ መንፈስ ቅዱስ ቅዱሳን ነቢያትን ስለመጻእያቱ መተንበይ እንዳስቻላቸው ማረጋገጡ ነዉ። ሆኖም ግን የመንፈስ ቅዱስና የሰዉ ልጆች ግንኙነት ከእርቅ በፊትና በኋላ አንድ አይነት አልነበረም ። ለዚህም ምክንያቱ በአዳም በደል ምክንያት በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተፈጠረዉ መራራቅ ነው። በኋላ እግዚአብሔር በልጁ ሞት በእርሱና በሰው መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ ካፈረሰ በኋላ እርቅ ሰላምም ሆነ (ኤፌ. 2፥14)። ይህን እርቅ ተከትሎ ብዙ ጥቅሞች ለሰዉ ልጆች ተገኝተዋል። ከነዚህም መካከል የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ለመቀበል መብቃት አንዱ ነው። ከላይ እንደተገለጠው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በዘመነ ብሉይ ይኖሩ ከነበሩ ቅዱሳን ጋር ቢኖርም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተገደበ ነበር።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ከጌታ ስቅለት በፊት በነበረው ሁኔታ ሆኖ “ ጌታችን ኢየሱስ ገና ስላልከበረ (ተሰቅሎ እርቅን ስላደረገ) መንፈስ ቅዱስ ገና አልወረደም ነበር” ብሏል። ከእርቅ በኋላ ግን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ለአማኒያንን ሁሉ ተሰጥቷቸዋል።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ

1.ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን መፈጸም።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን ሁሉ የምታከናውነው በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢር ፈጻሚነት ነው። ይህ ማለት ምን ማለት ነዉ? ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ሥጋ ተዋሕዶ በመከራ የተቀበለዉ ሞቱ የመዳናችን ተስፋ ነዉ ። ይህንን ተስፋ የምናገኘው ደግሞ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ነዉ። ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የምንላቸው ከምሥጢረ ጥምቀት እስከ ምሥጢረ ቀንዲል ያሉትን ሰባቱን ሲሆን ከእነዚህ መካከል አንድ ሕፃን ወይንም አንድ ከኢአማኒነት ወደ አማኒነት የተመለሰ ሰዉ ሊፈጽማቸው የሚገባቸው 3 የድኅነት ጸጋ ማግኛ ምሥጢራት አሉ። እነዚህም ምሥጢረ ጥምቀት ፣ምሥጢረ ሜሮንና ምሥጢረ ቁርባን ናቸው። ያለ እነዚህ ምሥጢራት የክርስቶስ የማዳን ጸጋ ለማንም ሊደርስ አይችልም። እነዚህ ምሥጢራት ለዘለዓለም ሕይወት እንደገና የምንታደስባቸው ናቸው /ቲቶ. 3፥3-5/። በምሥጢራቱ የሚገኘውን መታደስ ደግሞ የሚፈፅመዉ መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ይህንን እንዴት እንደሚያከናውን በእኛ አዕምሮ ሊመረመር ባይችልም ለሐዲስ ተፈጥሮ አማኞችን ሁሉ ሊያበቃ በሚችል መልኩ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ይፈጽማል። ለዚህም ነው ካህኑ የቀረበዉ ኅብስትና ወይን ወደ እውነተኛው የአምላክ ሥጋ እና ደም የሚቀየረው በመንፈስ ቅዱስ ፈቃሚነት መሆኑን በቅዳሴዉ መጀመሪያ ላይ “ይህቺ ቀን ምንኛ የምታስፈራ ናት መንፈስ ቅዱስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ መስዋዕቱን የሚሰዉርባት የሚያከብርባት” እያለ በማወጅ የሚያስረዳው ።

2.መንፈሳዊ ተጋድሎን ለመፈጸም የሚያበቃ ኃይልን ለአማንያን መስጠት

ያለ መንፈስ ቅዱስ እርዳታ መንፈሳዊ ተጋድሎን ከዳር ማድረስ አይቻልም። ሰብአዊ አቅም ፈተናን ተቋቁሞ ከዳር ለመድረስ የማይቻለው ደካማ ነው። ስለዚህ ከእለተ ጥምቀታችን ጀምሮ በጸጋዉ የሚነበኘን መንፈስ ቅዱስ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ኃይልንና ብርታትን በመስጠት እንድንጸና በማድረግ በሰብአዊ አቅማችን ልንደርስባቸው የማንችላቸውን ስኬቶች እንድንጎናጸፍ ያደርገናል።

በደቀመዛሙርቱ ሕይወት ላይ የምንመለከተው ይህንን ነው። የጌታ ደቀመዛሙርት ከበዓለ ሃምሳ ከጰራቅሊጦስ ዕለት በፊትና በኋላ ሁለት የተለያዩ ፍጡራን ነዉ የሚመስሉት። ከዕለተ ጰራቅሊጦስ በፊት የነበሩት ፈሪዎች ፣ደንጋጮች፣ እንዲሁም እምነታቸዉ ጎዶሎ የነበሩ ሲሆን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ከተቀበሉ በኋላ ግን የተጠቀሱት ድካሞች ሁሉ የጠፉላቸው አዲስ ፍጡራን ነው የሆኑት። ይህ ሁሉ የሆነዉ በተቀበሉት ጸጋ ነው።

ዛሬ የመንፈስ ቅዱስ ተራዳኢነት ከሁላችንም ጋር አለ። በጸጋው ሁላችንንም ይነበኘናል። እዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማያልፈው ግን በፊትም ቢሆን ሰውንና መንፈስ ቅዱስን ያለያየው የሰዉ በደል መሆኑ ነው። ዛሬም በደላችን ቅዱስ መንፈስ ከእኛ እንዲርቅ ያደርገዋል። እራሳችንን በምናኖርበት መንገድ መንፈስ ቅዱስ ይቀርበናል ወይ ይርቀናል። በንጽሕና ራሳችንን ጠብቀን በመኖር የጸጋዉ ተካፋይ ለመሆን ያበቃን ዘንድ ቸሩ ፈጣሪያችን ሁላችንንም ይርዳን። አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር